# የግንቦት 20 ትሩፋቶች

ሃይሉ ታከለ

05/26/13

## (ክፍል አንድ)

ኢትዮጵያ ላለፉት 22 ዓመታት ገደማ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ በምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ዙሪያ ከፍተኛ አፈፃፀም ማሳየቷ እሙን ነው፡፡ ለዚህ ውጤት መነሻ አገሪቱ የምትከተለው የፖለቲካ ሥርዓት ተጠቃሽ ነው፡፡ በዋናነት ደግሞ በህገ መንግሥቱ ውስጥ የሰፈሩት ህገ መንግሥታዊ የዴሞክራሲና የልማት ድንጋጌዎች እንደሆኑ ይታመናል፡፡ ይህ ሲባል ህገ መንግሥቱ በሰፊው የሕዝብ ተሳትፎ የተዘጋጀ ከመሆኑ ሌላ በህገ መንግሥቱ ውስጥ በሰፈሩት ድንጋጌዎች ላይ አገራዊ መግባባቱ እየዳበረ መምጣት፣ ለዴሞክራሲና ልማት ድንጋጌዎች ተግባራዊነት ቁርጠኛ መንግሥት መኖር በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአጭር ጊዜ ውስጥ ስር እየሰደደ እንዲሄድ ብሎም አገሪቱ ፈጣን ወደሆነ የልማት ጐዳና እንድትገባ አስችሏታል፡፡ ህገ መንግሥቱ አገሪቱ ፍትሃዊ የምጣኔ ሀብት ዓላማዎችን ማራመድ እንዳለባት በግልጽ ደንግጓል፡፡ ይህንን ዓላማ ለማረጋገጥ መንግሥት ዜጎች በአገሪቱ የሚገኘውን ሀብት በፍትሃዊነት ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አሠራር የመቀየስ ኃላፊነት ወድቆበታል፡፡

በልማት ወደ ኋላ የቀሩ ክልሎች በመንግሥት ልዩ እገዛ ተደርጐላቸው ጭምር የልማቱ ተጠቃሚነታቸው መረጋገጥ እንዳለበትም ህገ መንግሥቱ በማያሻማ መልኩ ደንግጓል፡፡
መንግሥት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብቶችን በሕዝብ ስም በይዞታው ስር በማድረግ ለዜጎች የጋራ ጥቅምና እድገት የማዋል ኃላፊነት እንዳለበት በህዳር ወር 1987 ዓ.ም የፀደቀው ህገ መንግሥት ያረጋግጣል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ህገ መንግሥቱ ሁሉም ዜጐች ለልማት መሠረት የሆኑ የትምህርትና የጤና አገልግሎቶች፣ የምግብ ዋስትና፣ የንፁህ መጠጥ ውኃ፣ የመኖሪያና የማህበራዊ ዋስትና የማግኘት መብት እንዲኖራቸው ይደነግጋል፡፡

ከዚህም ጋር በደርግ ሥርዓት ማንኛውም ዜጋ ተገፍፎ የነበረውን የግል ንብረት ባለቤት የመሆን መብት በመሠረቱ የናደ ሆኗል፡፡ በዚህም ሁሉም ዜጋ የግል ንብረት ባለቤትነት መብቱ በህገ መንግሥቱ ተከብሮለታል፡፡ ከሁሉም በላይ ህገ መንግሥቱ የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት የማይሸጥ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የጋራ ንብረት እንደሆነ በግልፅ አስፍሯል፡፡ በመሬት ጉዳይ የሕዝቦችን የጋራ

ተጠቃሚነት በጽኑ መሠረት ላይ ጥሏል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞም የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ የኢትዮጵያ አርሶና አርብቶ አደሮች መሬትን በነፃ የማግኘት፣ በመሬቱ የመጠቀምና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብታቸው ህገ መንግሥታዊ ዋስትና አለው፡፡

ዛሬ በኢትዮጵያ ሁሉም ዜጋ በማንኛውም የምጣኔ ሀብት እንቅስቃሴ ውስጥ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመከወን መብት እንዲሁም በመንግሥት ገንዘብ የሚካሄዱ ማህበራዊ አገልግሎቶችን በእኩልነት የመጠቀም መብታቸው ተረጋግጦላቸዋል፡፡

እኒህ ሁሉ የግንቦት ትሩፋቶች ናቸው፡፡

ሕዝቦች ለነጻነት ባደረጓቸው ትግሎች አምባገነኑን ሥርዓት ላይመለስ ገርስሰውታል፡፡ 22 ዓመታትም ተቆጥረዋል፡፡ በእነዚህ ጊዜያት መላ ኢትዮጵያውያን በሁሉም መስኮች አያሌ ድሎችን አስመዝግዋል፡፡ የድል ፍሬዎቹንም ማጣጣም ይዘዋል፡፡በህገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች መሠረት ሕዝቦች የኑሮ ሁኔታቸው የመሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብት እንዳላቸው በተግባር እየታየ መጥቷል፡፡ ዜጐች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ፣ በሚቀረፁ ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ አስተያየት የመስጠት መብት እንዳላቸውም በገሃድ እየታየ ይገኛል፡፡ የልማት እንቅስቃሴው ዋና ዓላማም የዜጐችን እድገትና መሠረታዊ ፍላጐቶችን ማሟላት በመሆኑ መንግሥት የሚያወጣቸው ፖሊሲዎችና የሚያደርጋቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የአገሪቱን ሕዝቦች ተጠቃሚነት መብት የሚያስከብሩ ስለመሆናቸው ከጋራ መግባባት ላይ  ተደርሷል፡፡ ዜጐች በመንግሥት ገንዘብ በሚካሄዱ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥት ባለፉት ሥርዓቶች ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ፍትህ ሳያገኙ የቆዩና በዚህም ምክንያት በልማት ወደ ኋላ የቀሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝ}ቦች በመንግሥት ልዩ ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ዋስትና ሰጥቷል፡፡ በዚህም መሠረት የፌዴራል መንግሥት ፍትሃዊ የልማት እንቅስቃሴ ከማረጋገጥ በተጨማሪ በልማት ወደ ኋላ የቀሩ ሕዝቦች መላ አቅማቸውን አሟጠው እንዲጠቀሙ ለማስቻል ልዩ ድጋፍ እየሰጣቸው ይገኛል፡፡ እገዛው በዋናነት የሚያተኩረው በማስፈፀም አቅም ግንባታ ላይ ነው፡፡ የመንግሥት አስተዳደርን የመገንባት፣ ቀልጣፋ አሰራርንና አደረጃጀት የመፍጠርና የሰው ኃይል አቅም ማጎልበትንም ይጨምራል፡፡

የግንቦት ትሩፋቶች የሆኑት የህገ መንግሥቱ ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ድንጋጌዎች ተጠቃለው ሲታዩ በነጻ ፍላጐት፣ በህግ የበላይነት፣ በእኩልነት፣ በጋራ ጥቅምና በራስ ፈቃድ ላይ የተመሰረተ አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ በጋራ የመገንባት ወሣኝነትን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ እንዲሁም

ዜጎች ንብረት የማፍራት፣ በመረጡት የሥራ መስክ የመሰማራት መብቶች በማረጋገጥ በነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት የሚመራ ፈጣንና ፍትሀዊ ልማት የማምጣት ጠቀሜታን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ የሕዝቦችን ልማታዊ አቅም ማሳደግና ለአገር ግንባታ ወሣኝ መሆናቸውንም ያሳያሉ፡፡ የዜጎችን የልማት ባለቤትነትና ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ማረጋገጥ የልማት እንቅስቃሴዎች ዋና ዓላማ መሆን እንዳለበት ከህገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ የክልሎችን እኩል የመልማት እድል ማረጋገጥና ልዩ ድጋፍ መስጠት መገንባት ለሚፈለገው በነፃ ፍለጎት ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ መረጋገጥ ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በራስ አቅምና በራስ ፍላጎት ነፃ አገራዊ ኢኮኖሚ መገንባት ለአገሪቱ ዘላቂ ሠላም፣ ዴሞክራሲና ልማት ወሳኝ መሆኑን የህገ መንግሥቱ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች በግልጽ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ህገ መንግሥቱ ልማት የመብት ጉዳይ መሆኑን ይገልጻል፡፡ የልማት እንቅስቃሴ ዋና ዓላማም የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል መሆኑ ተደንግጓል፡፡ የልማት አጀንዳ ደግሞ ለአገሪቱ ምን ያህል አንገብጋቢ እንደሆነ በግልጽ የሚታወቅ ነው፡፡ ይህንን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ መንግሥት በተለይ ፈጣን ልማት ማረጋገጥ የሞት ሽረት ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ እየተረባረበ ይገኛል፡፡ በደርግ ሥርዓት በአገሪቱ ለዓመታት ሰፍኖ የቆየው የእዝ ኢኮኖሚ ሥርዓት ተቀይሯል፡፡ በምትኩም የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ የአገሪቱ ምጣኔ ሀብት በነጻ የገበያ ሥርዓት እንዲመራ ማድረግ ብሎም የተፋጠነ እድገትን በማረጋገጥ አገሪቱን ከነበረችበት ፈታኝ የድህነትና ኋላ ቀርነት ችግር ማላቀቅን ዓላማው አድርጓል፡፡

በዚህም የገበያ መር የምጣኔ ሀብት ሥርዓትን ተከትሎ የኢንቨስትመንት፣ የንግድና የሥራ ሥምሪት ፖሊሲዎች ተነድፈው በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ በምጣኔ ሀብቱ ውስጥ ውስጥ የመንግሥት ዋና ሚና የተለያዩ የልማት ኃይሎችን በማቀናጀት መምራት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመሠረተ ልማት በማቅረብና የሰው ሀብት ልማት በማካሄድ ብሎም ፈጣንና ውጤታማ የመንግሥት አገልግሎቶችን በመስጠት ለግሉ ዘርፍ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠርና መደገፍ በአንፃሩ ደግሞ የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጮችን መዝጋት እና በግሉ ሴክተር የማይሰሩ የልማት ተግባራትን ማከናወን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ባለፉት ሥርዓቶች የግሉን ዘርፍ ቀጥተኛ ተሳትፎ ለመግታት ወጥተው የነበሩ ሕጎችና ደንቦች ተወግደዋል፡፡ ለውስጥም ሆነ ለውጭ ባለሀብቶች ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የንግድና ኢንቨስትመንት ፖሊሲ ሥር ነቀል በሆነ መልኩ ተለውጧል፡፡ በየጊዜው የተለያዩ እርምጃዎችም ተወስደዋል፡፡

ልቅ የሆነ የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓት ፈጣን፣ ዘላቂና ሰፊ መሠረት ያለው እድገት የማምጣት አቅም እንደሌለው እና ይልቁንም የሕዝብና የመንግሥትን አቅሞች ወደ ኪራይ ሰብሳቢነት እንዲሰማሩ

እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡ በመሆኑም በሂደት መንግሥት የማይተካ ልማታዊ ሚና የሚጫወትበት የነፃ ገበያ ሥርዓት መከተል በአንድ በኩል ህገ መንግሥቱን መሠረት በማድረግና የሕዝብ /የግሉ ዘርፍ/ እና የመንግሥት ተዋንያን በፍትሕዊ የገበያ ውድድር እየተመሩ ልማታዊ ኢንቨስትመንትን /ፕሮዳክቲቭ ኢንቨስትመንት/ የሚስፋፋበት በሌላ በኩል ደግሞ ገበያው የማይመልሳቸው የልማት ጥያቄዎች ደግሞ በተጠናና በተመረጠ ሁኔታ መንግሥት በራሱ በቀጥታ የሚሳተፍባቸውን አቅጣጫ እየተከተለ ይገኛል፡፡ በዚህም መሠረት መንግሥት የገበያ ጉድለቶችንና ተያያዥ የኪራይ ምንጮችን ለመዝጋት በመሠረተ ልማትና በሰው ሀብት ልማት ሰፋፊ ኢንቨስትመንቶችን በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህ አንፃር የፌዴራል መንግሥት የያዝነውን ዓመት የበጀት ድልድል በዋቢነት መጥቀስ ተገቢ ይሆናል፡፡ ከፌዴራል መንግሥት ከዓመቱ ጠቅላላ በጀት ውስጥ ግማሽ ያህሉ ለመንገድና ለትምህርት ዘርፎች የተመደበ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለኤሌክትሪክ ኃይል፣ ለቴሌኮምና ለባቡር መስመር ዝርጋታ በልማት ድርጅቶቹ አማካይነት ሰፋፊ ኢንቨስትመንት እያካሄደ ይገኛል፡፡ ይህ መሠረተ ልማትና የሰው ሀብት ልማት ኢንቨስትመንት የማስፋፋት ሥራ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ እንደ ልማታዊ መንግሥት ማከናወን ያለበት ቁልፍ ተግባር እንደሆነ ታምኖበት የሚካሄድ ነው፡፡

በዚህ መንገድ የገበያ ጉድለቱን በማጥበብ የኪራይ ምንጮችን ለማድረቅ እና እንዲሁም የማኑፋክቸሪንግ፣ የግብርናና የልማታዊ ኢንቨስትመንቶች ይበልጥ የሚበረታቱበት፣ መሬት፣ ብድርና ሌች ድጋፎች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እንዲያገኙ እየተደረገ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች የመንግሥት አገልግሎቶች ቀልጣፋና ግልጽ፣ ተገማችና ውጤታማ በማድረግ ልማታዊ ኢንቨስትመንቶቹ ይበልጥ አዋጭ የሚሆኑበትና የሚስፋፋበት ሁኔታ በየጊዜው እየጐለበተ ሄዷል፡፡ ይህም ሆኖ ሳለ ለኢትዮጵያ ፈጣን እድገት አስፈላጊ የሆኑ አንዳንድ ኢንቨስትመንቶች ገበያው ላያስተናግዳቸው እንደሚችል ይታመናል፡፡ ስለሆነም ፈጣን እድገቱ ሳይቆራረጥ ለማስቀጠል የዚህ ዓይነቱ የኢንቨስትመንት መስኮች በጥንቃቄ እየተጠኑና እየተመረጡ በቀጥታ በመንግሥት በራሱ ወይም ከግሉ ዘርፍ በሽርክና እንዲካሄዱ እየተደረገ ይገኛል፡፡

የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድ የመንግሥት ጣልቃ ገብነት ያስፈልጋቸዋል ተብለው የተለዩት የኢንዱስትሪ መስኮችም የማዳበሪያ፣ የብረታ ብረት ኢንጂነሪንግና የስኳር ኮምፕሌክሶች ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት ባለፉት 22 ዓመታት መንግሥት ልማታዊ የግል ኢንቨስትመንቶችን በማበረታታትና የኪራይ ሰብሳቢነት አማራጮችን በማጥበብ በግሉ ዘርፍ የማይሰሩ የልማት ሥራዎችን በማከናወን ሂደት ውሰን ሀብትን መሠረታዊ ችግሮችን በሚፈቱ ተግባራት ላይ በማዋል፣ የልማት ኃይሎችን በማቀናጀትና በመምራት፣ የሕዝብ ተሳትፎን በማጐልበት እና የግል

ኢንቨስትመንትን በማበረታታት ፈጣን፣ ቀጣይነት ያለውና ፍትሃዊ የምጣኔ ሀብት እድገትና ማህበራዊ ልማት ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

በህገ መንግሥቱ የተቀመጡ የልማት መብቶችና ዓላማዎችን ለማረጋገጥ የግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ተቀይሷል፡፡ የኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብትም የተመሰረተው በግብርና ላይ ነው፡፡ ከአጠቃላዩ የአገሪቱ ሕዝብ 84 በመቶው የሚኖረውም በገጠር ነው፡፡ የሚተዳደረውም በግብርና ሥራ ነው፡፡ አገሪቱ በብዛት ያላት ሀብትም /ጉልበትና መሬት / ከግብርናው ዘርፍ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው፡፡ ይህም ሆኖ የግብርናው ዘርፍ ባለፉት ሥርዓቶች እጅግ ትኩረት የተነፈገውና ሲበዘበዝም የኖረ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት ህገ መንግሥቱ በሚደነግገው ፍትሀዊና የሕዝብን ጥቅም ማዕከል ባደረገው ልማት መሠረት በመንግሥት ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቶት የአገሪቱን በአጠቃላይ በገጠር የሚኖረውን ሕዝብ የሚጠቅም ግብርናና ገጠርን ማዕከል ያደረገ የልማት ስትራቴጂ በሥራ ላይ ውሏል፡፡ ስትራቴጂው ፈጣን እድገት ለማረጋገጥ፣ ሕዝቡ ከልማቱ በላቀ ደረጃ እንዲጠቀም ለማድረግ፣ ኢትዮጵያን ከተመጽዋችነት ለማዳን እና በአገሪቱ የዳበረ የነፃ የገበያ ኢኮኖሚ ለመፍጠር ወሳኝ ሚና ይጫወታል ተብሎ ይታመናል፡፡ በተጨባጭ እየተረጋገጠ ያለውም ይኸው ነው፡፡

በዚህ መሠረት የገበያ ኢኮኖሚ ሥርዓትን በመከተል ግብርና ዋና የኢኮኖሚ እድገት ምንጭ ሆኖ የኢንዱስትሪ ልማቱ እንዲፋጠን ስትራቴጂው ከኢኮኖሚ መሠረተ ልማቶችና ማህበራዊ አገልግሎቶች ማለትም ትምህርት፣ ጤናና ውኃ እንዲሁም ከከተማ ልማት ጋር ትስስርና ተመጋጋቢነት ባለው አግባባ ተፈፃሚ በመሆን ላይ ነው፡፡ የግብርናው ዘርፍ በግብርና የሚተዳዳረውን ኅብረተሰብ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ያደረገ ነው፡፡ በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ በሚመራው የኢንዱስትሪ ዘርፍ ከተሳትፎና ከተጠቃሚነት አንፃር መንግሥት በዋነኛነት ለጥቃቅንና አነስተኛ ልማት ቅድሚያ ትኩረት ሰጥቷል፡፡

የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማት መስፋፋት የሥራ እድል በመፍጠር የዜጐች ገቢ፣ አቅምና የኑሮ ደረጃ ለማሳደግ ያስችላል፡፡ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ለልማታዊ የአገር ውስጥ ባለሀብት መፈጠር መሠረት እንደሚሆኑም ታምኖበታል፡፡ ጎን ለጎንም መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች በግሉ ባለሀብትና በመንግሥት በማስፋፋት የኢንዱስትሪ፣ የቴክኖሎጂና የሙያ አቅም እንዲዳብር እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይህም አቅጣጫ በህገ መንግሥቱ የተቀመጡ ፍትሃዊነት፣ የሕዝብ ተጠቃሚነትና የተሳትፎ ብሎም ነፃ አገራዊ ኢኮኖሚ የመገንባት ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ በህገ መንግሥቱ ከሰፈሩ ድንጋጌዎች ጋር የተቆራኙ የማህበራዊ ልማት ስትራቴጂና የመሠረተ ልማት ማስፋፋት ኘሮግራሞች ተነድፈው ባለፉት ዓመታት ተግባራዊ ሲደረጉ

ቆይተዋል፡፡ በዚህም በህገ መንግሥቱ የተቀመጡትን የሕዝብ ተጠቃሚነትንና አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የመገንባት ዓላማዎችን ለማሳካት ተችሏል፡፡

በማህበራዊ ልማት ዘርፍም መንግሥት መሠረታዊ ለውጦችን አድርጓል፡፡ የትምህርት ዘርፉ ሲታይ ባለፉት ሥርዓቶች ሽፋኑ አነስተኛ ሥርጭቱ ደግሞ አድሏዊ ነበር፡፡ መንግሥት በህገ መንግሥቱ የተደነገጉ ሁሉም ዜጎች ትምህርት የማግኘት መብታቸው እንዲረጋገጥና ተደራሽነቱም ፍትሃዊ እንዲሆን ለማድረግ የሚያስችል የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ አውሏል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ መንግሥት በመሠረታዊ ጤና አገልግሎትና በበሽታ መከላከል ላይ ያተኮረ ብሎም ሰፊውን ሕዝብ ለማገልገል ያለመና ማዕከል ያደረገ ፍትሃዊ የጤና አገልግሎት ሥርጭት የሚያረጋግጥ የጤና ፖሊሲ ነድፎ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡

የዜጎችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ሁሉም አካባቢዎች እኩል የመልማት እድል እንዲያገኙ ለማድረግ እና አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር ተፈላጊ ከሆኑት ሁኔታዎች ዋነኛው አስተማማኝ የመሠረተ ልማት አገልግሎት ማስፋፋት ነው፡፡ በኢኮኖሚ መሠረተ ልማቶች ዘርፍ መንግሥት ትኩረት የሰጠው ለመንገድ፣ ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት፣ ለኃይል ማመንጫ፣ ለቴሌኮምና ለባቡር ልማቶች ነው፡፡ መንግሥት እነዚህ የመሠረተ ልማት ሥራዎች ፍትሃዊነትንና የሕዝብ ተጠቃሚነትን ባረጋገጠ እና አገራዊ አንድነትን በሚያጠናክር ሁኔታ እንዲቀርቡ ለማድረግ የሚያስችል አቅጣጫ ቀይሶ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡

ለዘላቂ እድገትና ልማት እንዲሁም ፍትሀዊ የሕዝብ ተጠቃሚነት የሰው ኃይል ልማት ወሳኝ መሆኑ ይታመንበታል፡፡ ቀደም ሲል የነበረው የትምህርት ሥርዓት ሽፋን አነስተኛ፣ ኢ ፍትሃዊ እና ጥራቱና አግባብነቱ መሠረታዊ ችግር ነበረበት፡፡ በሽግግር ዘመኑ የመጀመሪያ ደረጃ የትምህርት ሽፋን 19 በመቶ ያህል ብቻ ነበር፡፡ ይህም በዋናነት በተወሰኑ አካባቢዎችና በከተሞች ላይ ብቻ ተወስኖ የቆየ ነበር፡፡ ባለፉት ዓመታት በተከናወነው ተግባር ይህንን ከመሠረቱ ለመቀየርና አገሪቱን  በትምህርቱ ዘርፍ በምሣሌነት የምትጠቀስ ለማድረግ ተችሏል፡፡

በመሆኑም ከህገ መንግሥታዊ ሥርዓት በ     ኋላ መንግሥት በገጠርና በከተማ በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በስፋት ገንብቷል፡፡ በዚህ ሂደት የኅብረተሰቡ ተሳትፎም የሚደነቅ ነበር፡፡ ባለፉት ስምንት ዓመታት /1997 - 2004/ ብቻ በመላ አገሪቱ 13 ሺህ የሚጠጉ የአንደኛ እና ከአንድ ሺህ በላይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተገንብተዋል፡፡ ይህ ውጤት ህገ መንግሥቱ የፈጠረው እድልና ህገ መንግሥቱን ተፈፃሚ ለማድረግ ዝግጁ የሆነ መንግሥት ብቻ ሊያረጋግጠው የሚችል ውጤት ነው፡፡ ባለፈው የበጀት ዓመት ላይ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቁጥር 30 ሺህ ገደማ ደርሷል፡፡

በተመሣሣይ ወቅት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቁጥር ከ1700 በላይ ለማድረስ ተችሏል፡፡ በዚህም የአንደኛ ደረጃ የትምህርት ተሳትፎን በተመለከተ ኢትዮጵያ በትምህርቱ ዙሪያ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች እንደሚያሳኩ ከሚጠበቁ ጥቂት አገራት መካከል ለማሰለፍ ተችሏል፡፡ ከፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ በፊት ኢትዮጵያ የነበራት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሁለት ብቻ የተማሪዎች የመቀበል አቅማቸውም ከሦስት ሺህ አይበልጥም ነበር፡፡

በአሁኑ ወቅት በመላ አገሪቱ 32 የመንግሥት ዩኒቨርሲቲዎች ተከፍተዋል፡፡ ዩኒቨርሲቲዎቹም 241 ሺህ ተማሪዎችን በቅድመ ምረቃ እና 24 ሺህ ተማሪዎችን ደግሞ በድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች በማስተማር ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ አኃዝ በግል ዩኒቨርሲቲዎች ያሉትን ሲጨምር የተማሪዎቹ ቁጥር ግማሽ ሚሊዮን ደርሷል፡፡ የከፍተኛ ትምህርቱን አግባብነት ለማሻሻልም ካለፉት ሦስት ዓመታት ጀምሮ ወደ ዩኒቨርሲቲ ከሚገቡት መካከል 70 በመቶ የሚሆነት የሣይንስና ቴክኖሎጂ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ቀደም ሲል የነበረው አግባብነትና ጥራት የጎደለው እንዲሁም በቀለም ትምህርት ላይ ያተኮረ የትምህርት ሥርዓትን በመሠረቱ የሚይየሩ ማሻሻያዎች በመንግሥት ተወስደዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን በማስፋፋት በርካታ ወጣቶች የቴክኒክና ሙያ ትምህርት በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡ ባለፉት ዓመታት በሙያው የተመረቁትም በከተሞች አካባቢ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች በመሰማራት የመንግሥት ዋነኛ የልማት አጀንዳ የሆነውን የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ በማሳካት ረገድ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ በህገ መንግሥቱ የተቀመጠ የዜጎች ትምህርት የማግኘት መብት በመሠረቱ የመለሱ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ ባለፈው የበጀት ዓመት ከመዋዕለ ህፃናት እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ በአጠቃላይ ሀያ ሚሊዮን የሚሆኑ ሕፃናትና ወጣቶች በትምህርት ገበታ ላይ መሆናቸው ሲታይ አገሪቱ በትምህርት ረገድ ምን ያህል ርቀት እንደተጓዘች በግልጽ የሚያሳይ ነው፡፡ ሌላኛው የግንቦት ትሩፋት፡፡